# የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ
# መመሪያን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 206/2013

የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003ን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ (ማሻሻያ) ቁጥር መመሪያ 206/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ማሻሻያ

የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ተሰርዘው እንደቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ተተክተዋል፤

"2/ የወጪ ማስማከሪያ

ሀ) በአገር ወስጥ ገንዘብ ለሚፈፀሙ ክፍያዎች የወጪ ማስማከሪያ ሞ/7/ በሣጥን የሚከናወን ክፍያ ሞ7/1፣ በባንክ በኩል የሚከናወን ክፍያ ሞ7/2 ወይም በኤሌክትሮኒክስ ክፍያ ዘዴ ማስተናገድ፣

ለ) በውጭ ምንዛሪ ለሚከናወን ወጪ የውጭ ምንዛሪ የወጪ ማስማከሪያ ሞ/8/ በተፈቀደ ኤሌክትሮኒክስ ዘዴ፤

ሐ) በገቢዎች ሚኒስቴር፣ በሆስፒታሎች በፍርድ ቤቶች በሞ/185 እና በሞ/85 ከተሰበሰበው ገንዘብ ወደ ሚደበኛ ገቢ ለማዘወርና ልዩነቱን ተመላሽ ለሚድረግ በቅድሚያ በሞ/186 እና ወሞ/86 ምዝገባና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በመመዝገብ ምዝገባወን ማወራረስ፣"

2. የመመሪያው አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5)፣ (6) እና (10) ተሰርዘው እንደቅደም ተከተላቸው በሚከተሉት አዲስ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4)፣(5)፣(6) እና (10) ተተክተዋል፤

"4/ **የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ**

ጥሬ ገንዘብ የሚይንቀሳቀስባቸው ወይም ጥሬ ገንዘብ ነክ ያልሆኑ ሜቸቸውም የሂሳብ ክንውኖች በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ መሂ/9 ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የምዝገባ ማዘዣ ሚፀም አለባቸው፡፡

5/ **የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ**

በየዕለቱ የተሰበሰበ ገንዘብ በገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ መሂ/64 ተጠቃሎ ወይም ከመሂ/1 ወደ መሂ/64 በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ በማጠቃለል ገቢ መደረግ አለበት፡፡

6/ **በገቢ ማለያ ቁጥር የተለየ የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ**

በገንዘብ ሰብሳቢዎች የተሰበሰበ ጥሬ ገንዘብ የገቢ ማለያ ቁጥር የተለየ የገቢ ደረሰኝ ማጠቃለያ መሂ/65 ተዘርዝሮ ለዋና ገንዘብ ያዥ በመሂ/64 እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ጭምር መተላለፍ አለበት፡፡

**የሂሳብ ሪፖርት**

10/ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርቶችን በአገር ወስጥ ገቢ/እርዳታ/የብድር ሂሳብ መሂ/21፣ መደበኛ በጀት ወጪ ሂሳብ ሪፖርት መሂ/22፣ በካፒታል በጀት ወጪ ሂሳብ ሪፖርት መሂ/23፣ በገንዘብ ዝወውር ሂሳብ ሪፖርት ክፍል 1 እና 2 መሂ/24፣ በተሰብሳቢ ሂሳቦች መሂ/25፣ በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት መሂ/26 እና በሂሳብ ማማዘኛ ሪፖርት መሂ/27 እንዲሁም ሁሉንም የሪፖርት ፎርሞች በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካኝነት ጭምር ሪፖርት ማዘጋጀት አለባቸው፡"

3. <u>**መመሪያ የሚፀናበት ቀን**</u>

ይህ መመሪያ ከህዳር 19 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 15 ቀን 2012 ዓ.ም**

**አህመድ ሺዴ**
**የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር**